# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መመሪያን ለሦሥተኛ ጊዜ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

በባለስልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ እንዲሁም መመሪያ ልዩልዩ ድንጋጌዎች በዘመናዊ ግብይቱ ለሚተፉ ተዋናዮች የተሰጠው የማጣሚት መብት ተግባራዊ የሚሆንበትን ሥርዓት በግልፅ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መመሪያ ቁጥር 537/2013ን ለሦሥተኛ ጊዜ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 34/2/ /እንደተሻሻለው/ መሠረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መመሪያን ለሦስተኛ ጊዜ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 585/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

በመመሪያው ክፍል አስር ከአንቀጽ 19 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 20 ተጨምሯል፡፡

20/ **የግብይት ተሳታፊዎች አቤቱታ ስለሚጣበት ሁኔታ**

1/ በባለስልጣኑ ወሳኔ ላይ አቤቱታ አቅርቦ የመሠማት መብት በባለስልጣኑ አዋጅና መመሪያ ልዩልዩ ድንጋጌዎች የተሰጠው ሰው ውሣኔው በደረሰው በ30 ቀናት ወስጥ ለአስተዳደር ችሎቱ በማቅረብ ማጣሚት ይችላል፡፡

2/ አስተዳደር ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ከሰማ በኋላ የባለሥልጣኑን ውሣኔ ሊያፀና፣ ሊያሻሽል፣ ሊሽር ወይም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ወደ ሚመለከተው የሥራ ክፍል ሊመራው ይችላል፡፡

3/ ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ አንቀጽ መሠረት ችሎቱ በሚጠው ወሳኔ የማይስማማ ተከራካሪ ወገን ለባለስልጣኑ ቦርድ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

4/ በባለስልጣኑ አስተዳደር ችሎት የሚቀርብ የማጣሚት አቤቱታም ሆነ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ለባለሥልጣኑ ቦርድ የሚቀርብ ይግባኝ በጽሁፍ ሆኖ በዚህ ክፍል በተወሰነው የጉዳዮች አወሳሰን ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች እንደአግባብነ ታቸው የሚመራ ይሆናል፡፡

## 3. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር 24 ቀን 2004 ዓ.ም ፀደቀ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ